## 5.ማጠቃለያና የተሰጡ አቅጣጫዎች፡-

- በከተማና ገጠር የሚቀርቡ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን የመቀበልና የመገምገም ስራ የተቀመጡ ሀገራዊ እና ክልላዊ ህጎችን፤ አዋጆችና ደንቦችን መሰረት ተደርጎ በዲሲፕሊን የሚፈፀም ተግባር መሆኑ ይታወቃል፡፡ይሁን እንጂ ከዚህ ተግባር አንጻር በከተሞች በተለይ የአገልግሎት ኢንቨስትመንት ዘርፎች ለመሰማራት ጥያቄ በሚያቀርቡ ባለሃብቶች/ድርጅቶች ዙሪያ በተቋማት መካከል መገፋፋት በመስተዋሉ በተግባር ያሉትን ህጎች በአግባቡ በመፈተሽ በህግ ባለሞያዎች በኩል ወጥ የመፍትሄ ሀሳቦች እስከሚሰጡ ድረስ ወደ ክልላችን የሚመጡ ባለሃብቶችና ፕሮጀክቶችን የመቀበል፤ በባለሀብቱ የሚቀርቡ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ክልላዊ የኢንቨስትመንት ፍኖተ ካርታንና የእቅድ ስንሰለቱን መሰረተ ያደረጉ መሆናቸውን ፡እንዲሁም የፕሮጀክቶችን አዋጭነት ጥናቶች በየደረጃው በሚገኙ የኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ተቋማት ሙያዊ በሆነ መንገድ የመገምገም፤ አስተያየት እየተሰጠባቸውና በደረጃ እየተለዩ በመሸኛ ደብዳቤ በየደረጃው ለሚገኙ የከተማና መሰረተ ልማት ተቋማት እየተላኩ የከተሞችን እድገትና ፕላን መሰረት በማድረግ፤ ለሚቀርቡ ፕሮጀክቶች መሬት መኖሩ በተቋማቱ ተረጋግጦና ሳይት ፕላን እየተዘጋጀላቸው በየደረጃው ባሉት የኢንቨስትመንት ቦርድ አባላት ውሳኔ



ቁጥር 2
Amhara National Regional State Industry and Investment Bureau

Scanned with AnyScanner

**3. የአገልግሎት ኢንቨስትመንት ዘርፍ ( ሆቴል፤ሎጂ፤ሞቴል፤ሪዞርት፤ጤና፤ትምህርት፤ስፖርት ተቋማት፤ባለኮከብ ሆቴል ፤ዲፖ ወዘተ ማወዳደሪያ መስፈርት፤-**

(1) የፕሮጀክቱ የ3 ተከታታይ ወራት የባንክ እንቅስቃሴ ------40%

(2) ፕሮጀክቱ የሚፈጥረው የሥራ ዕድል ብዛት------------ 30%

(3) የአካባቢውን ማኅበረ-ሰብ በመሠረተ-ልማት እና ሌሎች አገልግሎቶች ተጠቃሚ ለማድረግ በፕሮጀክት ሀሳብ ዕቅድ ያካተተ---- 10%

(4) ለአረንጓዴ ልማት እና ለአካባቢ ጥበቃ እንክብካቤ አስተዋፅዖ ለማድረግ በፕሮጀክት ሃሳቡ ያካተተ ከሆነ--- 5%

(5) የባለሀብቱ የሥራ ልምድ -----10%

(6) በፕሮጀክት ሀሳቡ ለሠራተኞች ምቹ አካባቢ ለመፍጠር ዕቅድ ያካተተ (የምግብ፣ የጤና እና የመጠለያ አገልግሎቶች የሚያቀርብ)-- 5%

Scanned with AnyScanner